# በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት ለተከራዮች የሚሆኑ መረጃ እና ግብዓቶች

## ከቤት የማስወጣት ጊዜያዊ እገዳ በጁላይ 24, 2020 ያበቃል

**የገቢ ምንጭ ከሌልዎት**
**ስለ ኪራይ ቅነሳ ወዲያውኑ ለእርስዎ PHA ያነጋግሩ**

- ባለመክፈል ምክንያት ከቤት ማባረርን ይከላከሉ
- የኮቪድ-19 (COVID-19) መረጃ እና ደህንነት ጭንቀቶች
- ለቤተሰብ እና ለጾታዊ ጥቃት መከላከያዎች
- አገልግሎቶች እና ግብዓቶች

## ኪራይ ባለመክፈል ምክንያት ከቤት ማባረርን ይከላከሉ

➢ **ከጁላይ 24, 2020 በኋላ ኪራይ ባለመክፈል ምክንያት ከቤት የማባረር ማሳወቂያ ሊደርሰኝ ይችላል?**
አዎ። ለረጅም ጊዜ ከቤት የማባረር ጊዜያዊ ማስተላለፍ በመንግስት ወይም የአካባቢ ህግ ስር ተግባር ውስጥ ካልዋለ፣ ኪራይዎን ካልከፈሉ ወይም ዳግም ክፍያ ስምምነት ውስጥ ካልገቡ ከጁላይ 25, 2020 ጀምሮ፣ የእርስዎ PHA ወይም አከራይ ከቤት የማባረር ማስታወቂያ ሊሰጥዎት ይችላል። በፌደራል ህግ በ CARES ህግ ስር በጊዜያዊ ማስተላለፍ መጨረሻ የተሰጠው ከቤት የማባረር ማስታወቂያ፣ ተከራዩን ንብረት ለማስወጣት ቢያንስ 30 ቀናት ይሰጠዋል፣ ይሁንእንጂ በመንግስት ወይም በአካባቢ ህግ ረጂም ማስታወቂያ ጊዜ ሊያስፈልግ ይችላል። ከቤት የማባረር ማስታወቂያ ከደረስዎ፣ ከቤት የማማባረር ስራ የአካባቢዎን ሂደት መከተል አለብዎት። በስህተት ከቤት መባረርዎ ከተሰማዎ፣ የአካባቢ የህግ እገዛ ድርጅትዎ ወይም የማህበራዊ አገልግሎት ወኪሎችዎን ያነጋግሩ። እርስዎ የድጎማ ኪራይ ተሳታፊ ከሆኑ፣ የአካባቢዎ PHA ማነጋገር ይችላሉ። እርስዎ የ መንግስት ቤት ተሳታፊ ከሆኑ፣ በኮንትራትዎ ውስጥ እንደተጠቀሰው የአቤቱታ ሥርዓት መብት አለዎት።

➢ **የሚገባኝን ኪራይ ካልከፈልኩ ከቤት መባረርን ን ለማስወገድ ምን ማድረግ አለብኝ?**
ኪራይ አሁንም መከፈል አለበት እና ካልተከፈለ ይከማቻል። ያልተከፈለ ማንኛውም ኪራይ ካልዎት፣ እታች ያሉ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች ወዲያውኑ ከእርስዎ PHA ይነጋገሩ፡-

(1) እርስዎ ኪራይዎን በጊዜው ለመክፈል ያስቸገርዎ **የገቢ መቀነስ ወይም በሁኔታዎች ላይ ለውጥ** ከነበርዎ፣ ገቢዎን ዳግም ለማስመስከር የእርስዎን PHA ይጠይቁ።

- ✓ ለ መንግስት ቤት ተሳታፊዎች እና ለ የድጎማ ኪራይ ተሳታፊዎች ለሁለቱም፣ PHA የአሁኑ ገቢዎ ይከልሱ እና ለውጡን ለማንጸባረቅ ኪራይዎን ያስተካክላሉ።
  - ○ **ጠቃሚ ምክሮች**! የገቢ ለውጡ ወዲያውኑ ሪፖርት ካልተደረገ፣ ስለ ተከታታይ የኪራይ ማስተካከያዎች (አንዳንዱ ሊፈቅዱላቸው ይችላሉ፣ አንዳንዱ ላይፈቅዱላቸው ይችላሉ) ፖሊሲዎቻቸው PHAን ይጠይቁ።
- ✓ ለአነስተኛ የኪራይ ክፍያ ችግር ነጻ ማድረግ ብቁ መሆኑዎን PHAን መጠየቅ ይችላሉ። ሁሉም PHA አነስተኛ የኪራይ ክፍያ ችግር ነጻ ማድረጊያዎች ለማቅረብ ያስፈልጋሉ። የ PHA ስለ ክፍያ ችግር ነጻ ማድረጊያዎች የአካባቢ ፖሊሲዎች መረጃ የ PHA መግቢያ እና ቀጣይ የይዞታ ፖሊሲ (Admission and Continued Occupancy Policy (ACOP)) መከለስ ይችላሉ ወይም ከ PHA ጋር በቀጥታ መገናኘት ይችላሉ።

(2) ሁሉም የ መንግስት ቤት ተሳታፊዎች እና የ ድጎማ ኪራይ ተሳታፊዎች ከጁላይ 24, 2020 የኋላ ኪራይ በጥቅል ለመክፈል አማራጭ አላቸው። የእርስዎ PHA እና አከራይዎ በኤፕሪል፣ ሜይ፣ ጁን እና ጁላይ 2020 ወራት መከፈል የነበረበት ኪራይ የዘገዩ ክፍያዎች ወይም ወለድ ማስከፈል አይችልም።

(3) ያለፈው ኪራይ ጥቅል ሂሳብ ካልከፈሉ፣ ለማንኛውም ያለተከፈል የኪራይ ሂሳብ ወደ **ዳግም ክፍያ ስምምነት** መግባት የሚችሉ ከሆነ የእርስዎ PHA ወይም የእርስዎ አከራይ (የድጎማ ኪራይ ተሳታፊ ከሆኑ) ይጠይቁ። *ስለ ዳግም ክፍያ ስምምነቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ጿታች ይመልከቱ።*

- **ጠቃሚ ምክሮች!** የ $1,200+ ፌደራል የኢኮኖሚክ ተጽዕኖ ክፍያ (ማነቃቂያ ክፍያ (stimulus payment)) በገቢ ሂሳብዎ ውስጥ አልተካተተም። ባልተከፈለው ኪራይ ለማገዝ ይህ እንደ ግብዓት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። አብዛኖቹ የዩ ኤስ ዜግነት ያላቸው ነዋሪዎች ለዚህ ክፍያ ብቁ ናቸው። የማነቃቂያ ክፍያ ካልደረስዎት፣ እባክዎ የክፍያዎ ደረጃ ለማረጋገጥ ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ እና ቀላል ቅጽ ይሙሉ። https://www.irs.gov/coronavirus/get-my-payment።
- **ጠቃሚ ምክሮች!** በ CARES ህግ የቀረበው ተጨማሪ በሳምንት የ $600 ጊዜያዊ ስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች በገቢ ሂሳብዎ ውስጥ አልተካተተም። ይህንን ተጨማሪ ጥቅም ከደረስዎት፣ ይህ ላልተከፈል ኪራይ ለማገዝ እንደ ግብዓት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ስራዎ ካጡ እና ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ገና ካላመለከቱ፣ ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ በ፦ www.usa.gov/unemployment; www.careeronestop.org/LocalHelp/UnemploymentBenefits. ማስታወሻ፦ በ CARES ህግ የቀረበው ተጨማሪ በሳምንት የ $600 ጊዜያዊ ስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች በጁላይ 31, 2020 ያበቃል እና አሁን ማመልከት ይህንን ተጨማሪ የክፍያ ጥቅማ ጥቅም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም፣ ይሁንእንጂ አሁንም ለመደበኛው ስራ አጥነት መድህን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

(4) ለኪራይ፣ መገልገያዎች እና ሌላ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለማገዝ የእርስዎ PHA ስለ **አካባቢ ግብዓቶች** ሊያውቅ ይችላል።
እንዲሁም ከማንኛውም ስልክ 211 መደወል ወይም ለአደጋ ጊዜ ፋይናንሳዊ እገዛ መረጃ ለማግኘት 211.org መጎብኘት ይችላሉ። እባክዎ ሊሆኑ ለሚችሉ ዝርዝር ግብዓቶች በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የአገልግሎቶች እና ግብዓቶች ክፍል ይመልከቱ።

### ➢ ዳግም ክፍያ ስምምነት ማለት ምን ማለት ነው እና ከቤት ማስወጣትን ለማስወገድ ደንቦቹ ምን ይሆናሉ?

የዳግም ክፍያ ስምምነት ያለፈ ያልተከፈለ የኪራይ መጠን እና በእያንዳንዱ ወር እርስዎ መክፈል ያለብዎትን መጠን እና ለስንት ወር ያህል እንደሚከፍሉት (ለምሳሌ እርስዎ $500 ዕዳ ካልዎ እና ከመደበኛ የኪራይ ክፍያዎ በእያንዳንዱ ወር ተጨማሪ $50 ለ 10 ወራት ለመክፈል ከተስማሙ) በእርስዎ እና በ PHA (ለመንግስት ቤት ተሳታፊዎች) ወይም አከራይዎ (ለድጎማ ኪራይ ተሳታፊዎች) የተጻፈ እና የተፈረመ ኮንትራት ነው። ዳግም ክፍያ ስምምነት መግባት የ PHA ወይም የአከራዩ መብት ነው። የዳግም ክፍያ ስምምነት ዘግይተው መክፈል እና አለመክፈል የመከራየት እና/ወይም ድጋፍ ማቋረጥ ሊያስከትል ይችላል። ለ መንግስት ቤት ተሳታፊዎች፣ የዳግም ክፍያ ስምምነት ውሎች በ PHA መግቢያ እና በቀጣይ ይዞታ ፖሊሲ (ACOP) እና በዳግም ክፍያ ስምምነት ጽሑፍ ውስጥ ተዘርዝሯል። የዳግም ክፍያ ስምምነት ውሎች ለመወሰን የድጎማ ኪራይ ተሳታፊዎች በቀጥታ ከአከራዩ ጋር መስማማት ያስፈልጋቸዋል።

## የኮቪድ-19 (COVID-19) መረጃ እና ደህንነት ጭንቀቶች

### ➢ ለኮቪድ-19 (COVID-19) ምርመራ ፖዘቲቭ ሆኘ ከተገኘሁ ምን ማድረግ አለብኝ?

የምርመራዎ ውጤት ፖዚቲቭ መሆኑን ካሳየ ወይም ለሌላ ፖዚቲቭ ውጤት ያለው ሰው ከተጋለጡ ሌሎችን ተከራዮች እና ሰራተኞች ደህንነትን ለማገዝ የእርስዎ PHA ራስ ሪፖርት እንዲያደርጉ ሊጠይቅዎ ይችላል። ስለ ምርመራ የእርስዎን PHA ወይም አከራይ ለመንገር አያስፈልግዎትም። ይሁንእንጂ፣ ይህንን መረጃ ማጋራት ሰራተኞችን እና እርስዎ የተገናኙዋቸው ሌሎች ሰዎች ለመከላከል ሊያግዝ ይችላል።

- **ሌሎች ተከራዮች ለኮቪድ-19 (COVID-19) ምርመራ ፖዚቲቭ መሆናቸውን የማወቅ መብት አለኝ?**

የእርስዎ PHA ንቁ የኮቪድ-19 (COVID-19) ምርመራን ከእርስዎ ጋር ማጋራት የለበትም። ይሁንእንጂ፣ አንዳንድ PHAዎች በህንጻቸው ውስጥ የሆነ ሰው ለኮቪድ-19 (COVID-19) ምርመራ ፖዚቲቭ መሆኑን ካወቁ ተከራዮችን ማሳወቅ ይችላል።

- **ስለ ንብረት አስተዳደር እና ጥገና ጥያቄዎች ወይም ጭንቀቶች ካሉኝ'ስ?**

ስለ ንብረት አስተዳደር እና የጥገና ጥያቄዎች የእርስዎ PHA ወይም አከራይ ለመነጋገር መቀጠል አለብዎት። ለአስቸኳይ ጊዜ ላልሆኑ ጭንቀቶች ወይም ጥያቄዎች ምላሾች የተገደቡ ወይ የዘገዩ ሊሆኑ ይችላሉ። የኮቪድ-19 (COVID-19) ስርጭት ለመቀነስ አንዳንድ PHA ጽሕፈት ቤታቸውን በአካል ዘግተዋል፣ ይሁንእንጂ በቴሌፎን፣ ኢሜይል ወይም የመስመር ላይ ፖርታላቸውን ይገኛሉ። አንዳንድ ጽሕፈት ቤቶች በቀጥታ ድጋፍ ቀንሷል እና/ወይም ለአስቸኳይ ጉዳዮች ብቻ ምላሽ በመስጠት ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ያላቸው በህንጻዎ ላይ ወይም በንብረት አስተዳደር ጽህፈት ቤት አካባቢ የተለጠፉ በራሪ ጽሑፎች ወይም መልእክቶች ካሉ፣ ይፈትሹ።

- **በህንጻየ ውስጥ የተለከፉ ግለሰብ(ቦች) ካሉ PHA የኔን ክፍል በሙያዊ ማጽዳት ይፈለግበታል?**

አይ፣ PHA የጋራ ስፍራዎች የማጽዳት ሓላፊነት ሲኖረው እርስዎ ደግሞ ክፍልዎን የማጽዳት ሃላፊነት አለብዎት።

- **በዚህ ወቅት የኔ የነዋሪ ምክር ቤት ለተከራዮች እንዴት መደገፍ ይችላል?**

የነዋሪ ምክር ቤቶች ከአካባቢ ወኪሎች አጋርነት በማድረግ፣ ጥናቶችን በማካሄድ እና በኮቪድ-19 (COVID-19) ስራዎች ላይ የነባሪ ግብዓት በመሰብሰብ እና ለ PHA ሊቀርቡ የሚችሉ ችግሮች እና የአካባቢ ግብዓቶችን ዝርዝር አንድ ላይ በማድረግ ኮቪድ-19 (COVID-19) ጋር የተያያዙ ጥረቶችን ሊደግፍ ይችላል። የነዋሪ ምክር ቤቶች ምናባዊ ስብሰባዎች እና ስልጠናዎች እና አስፈላጊ መረጃን ለመገናኘት (እንደ Twilio፣ Simpletexting ወይም eztexting የመሳሰሉ) ብዙ የጽሑፍ መላላክ አገልግሎት ለማስተናገድ ለቪድዮ ኮንፈረንሲንግ ቴክኖሎጂ ምዝገባ (ለምሳሌ፦ Zoom) ለመግዛት የተከራይ ተሳታፊነት ገንዘቦችን መጠቀም ይችላሉ።

- **በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ለመንግስት ቤት የማህበረሰብ አገልግሎት እና የራስ ብቃት መመዘኛ (CSSR) ለማሟላት ካልቻልኩ ምን ችግር አለው?**

CSSR የሚመለከተው ለ<u>መንግስት ቤት ተሳታፊዎች</u> ብቻ እንጂ ለ <u>ድጎማ ኪራይ ተሳታፊዎች</u> አይመለከትም። የእርስዎ PHA የኮቪድ-19 (COVID-19) የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ውድቅ ማድረግ ተቀብሎት ሊሆን ይችላል። የእርስዎ PHA ውድቅ ማድረግ መቀበሉን እና ለማህበረሰብ አገልግሎት እና የራስ ብቃት ተግባሮች እና ወደ ስምምነት መምጣት መመሪያ ለማግኘት ለእገዛ ወደ እርስዎ PHA የነዋሪ አገልግሎት ሰራተኛ አስተባባሪ መገናኘቱን ይጠይቁ።

- **ወደ ክፍሌ ከመግባቱ በፊት የግል መከላከያ መሳሪያ (PPE) ለመልበስ ተቆጣጣሪዎች ያስፈልጉኛል?**

አዎ፣ ያለ PPE ለምሳሌ የፊት መሸፈኛ ወይም ጭምብል ወደ ቤትዎ የሚገባ የ PHA ሰራተኛ ላይ ምቾት ካልተሰማዎት፣ እባክዎ ከመንግስት ወይም የአካባቢ የጤና ባለሙያዎች የተሰጠውን የ CDC መመሪያውን እና ምክሮችን መከተል እንዳለባቸው የ PHA ሰራተኛውን በትህትና ይጠይቁ።

## ለቤተሰብ እና ለጾታዊ ጥቃቶች መከላከያዎች

- **VAWA ምንድነው? እና በ VAWA መከላከያዎች ሽፋን አለኝ?**
  - የሴቶች ህግ ተጻራሪ ጥቃት (VAWA) ለቤተሰብ ጥቃት፣ ለትውውቅ ጥቃት፣ ለጾታዊ ዓመጽ እና ማድባት (የ"VAWA ወንጀሎች" ተብለው የሚጠቀሱ) ተጎጂዎች ጥበቃዎችን ይሰጣል።
  - ጾታ ሳይለይ መከላከያዎች ይገኛሉ።

- **በኮቪድ-19 (COVID-19) ውሸባ ምክንያት የኔ የ VAWA መከላከያዎች ተለውጧል?**
  - አይ፣ የ VAWA ወንጀል ተጎጂ ከሆኑ፣ መከላከያዎችዎ በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት ተመሳሳይ ሆነው ይቆያሉ። የቤተሰብ ጥቃት፣ ለትውውቅ ጥቃት፣ ለጾታዊ ዓመጽ እና ማድባት መሰረት ወይም ቀጥታ ውጤት እገዛ አይከለከሉም ወይም እገዛው አይቋረጥም።
  - በተጨማሪ፣ የ VAWA ወንጀሎች ተጎጂ በመሆንዎ አደገኛ ወይም የኮንትራትዎ ተደጋጋሚ ጥሰት ወይም ለእርስዎ እገዛ፣ የተከራይነት ወይም ይዞታ መቋረጥ መልካም ምክንያት ሊታሰብ አይችልም። ይሁንእንጂ፣ ለሌሎች ተከራዮች ትክክለኛ እና የማይቀር ስጋት ሲኖር PHA ወይም የቤቱ ባለቤት ጉዳይ በጉዳይ መሰረት በማድረግ አድራጎቶችን ይገመግማል።

- **በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት መጎሳቆልን ለማምለጥ ከቀየርኩ ምን ችግር አለው?**
  - ከእርስዎ PHA የአስቸኳይ ጊዜ ማዛወር መጠየቅ ይችላሉ። እያንዳንዱ PHA ብቁ ሰው ማነው፣ ምን ዓይነት ሰነድ እንደሚያስፈልግ(ካለ)፣ PHA ምስጢራዊነትን እንዴት እንደሚጠብቅ እና PHA የአደጋ ጊዜ ማዛወር ጥያቄዎችን እንዴት ማስኬድ እንደሚችል በዝርዝር የሚገልጽ የአደጋ ጊዜ ማዛወር ዕቅድ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

- **ለአደጋ ጊዜ ማዛወር ጥያቄ ምን ዓይነት ሰነድ ያስፈልገኛል?**
  - PHAዎች የቃል መግለጫ ሊቀበሉ ይችላሉ፣ ስነድን መጠየቅ ላያስፈልጋቸው ይችላል። የሰነድ መመዘኛዎች በ PHA የአስቸኳይ ጊዜ የማዛወር ዕቅዱ ውስጥ ይካተታል።
  - ሰነድ ካስፈለገ፣ ከሚከተሉት ማንኛውም አማራጮች ምርጫዎን ሊያቀርቡ ይችላሉ፦ (Form HUD-5382) በመጠቀም ራስዎን ማረጋገጥ **ወይም** ከማጎሳቆል ጋር ለእርስዎን እገዛ ያደረገ ማንኛውም ሰው (ሰራተኛ፣ ወኪል ወይም የተጎጂ አገልግሎት ሰጪ በጎ አድራጊ፣ ጠበቃ ወይም ይህክምና ባለሙያ ወይም የአእምሮ ጤና ባለሙያ) **ወይም** አስተዳደራዊ መዝገብ (የፖሊሲ ሪፖርቶች እና የክልከላ ትእዛዞች አካቶ)።

- **በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት አጥቂው ከክፍሌ ማስወጣት ብፈልግ ምን ችግር አለው?**
  - የእርስዎ የ VAWA መብቶች በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅትም የተጠበቁ ናቸው። የቤተሰቡ አባል በቀጥታ ከ VAWA ወንጀል ጋር የተያያዘ በወንጀል ተግባር ውስጥ ከተሳተፈ፣ ለእርስዎ ሊኖሩ የሚችሉ አማራጮችን ለመወያየት የእርስዎ PHA ወይም የቤቱ ባለቤት ያነጋግሩ።

- **በአጋጣሚ ፈጻሚው የቤተሰቡ አባል ከሆነ አስተማማኙ እና በጣም ምስጢራዊ የሆነ የመገናኛ መንገድ ምንድነው?**
  - እባክዎ PHA ከእርስዎ ጋር የሚገናኙበት አስተማማኝ መንገድ ያሳውቁት። ከ PHA ጋር የሚደረጉ ሁሉም መረጃ ማጋራት በጥብቅ ምስጢር መሆን አለባቸው።

- **ይህ ማለት የ VAWA ተጎጂ አይባረርም ወይም እገዛቸውን አይቋረጥም ማለት ነው?**
  - አይ፣ በ VAWA ወንጀል መስረት ያላደረጉ ጥሰቶች VAWA ለ PHA ወይም የቤቱ ባለቤት ከቤት ማባረር ወይ እገዛ ከማቋረጥ ሊከለክለው አይችልም። PHA ወይም የቤቱ ባለቤት እንደሌሎች ተከራዮች በተመሳሳይ እርስዎን መያዝ ይገባዋል። PHA/ባለቤቱ ለከፍተኛ ወይም በ VAWA ላይ መሰረት ያደረገ ተደጋጋሚ የኮንትራት ጥሰቶች ወይም PHA/ባለቤቱ ለሌሎች ተከራዮች ትክክለኛ እና የማይቀር ስጋት ሲኖር አሁንም ሊያባርርዎ ይችላል።

- **ስለኔ VAWA የቤት መከላከያዎች PHA ሊነግረኝ ያስፈልገዋል?**
  - አዎ፣ የእርስዎ PHA መግቢያ ወይም እገዛ ከተከለከሉ ሳይቆዩ ወይም እገዛ ከተሰጥዎ እና የእገዛ ማቋረጥ ማሳወቂያ ሲደርሶ የእርስዎ VAWA መከላከያዎች ማሳወቅ አለባቸው።
- **ከተናደድኩ፣ በችግር ውስጥ ካለሁ ወይም አሁን ለማንኛውም ሰው ለማነጋገር ከፈለኩ ምን ማድረግ አለብኝ?**
  - ስለ ደህንነቱ ያልተጠበቀ እርካሽ ግንኙነት በተመለከተ እገዛ፣ በ 1-800-799-7233 ነጻ የስልክ መስመር ለብሔራዊ የቤተሰብ ጥቃት መደወል ይችላሉ ወይም መስማት ለተሳናቸው ሰዎች 1-800-787-3224 (TTY) ወይም ወደ 22522 LOVEIS ብለው ጽሁፍ ይላኩ።
  - ስለ ጾታዊ ዓመጽ በተመለከተ እገዛ ለማግኘት፣ በ 1-800-656-4673 ብሔራዊ የጾታ ጥቃት ነጻ መስመር (RAINN) መገናኘት ይችላሉ።
- **ተጨማሪ ግብዓቶች፦**
  - ስለ ማድባት በተመለከተ እገዛ ለማግኘት፣ በ https://www.victimsofcrime.org/our-programs/stalking-resource-center የወንጀል ተጎጂ ብሔራዊ ማእከል የማድባት ግብዓት ማእከልን ይጎብኙ።
  - ለእያንዳንዱ ግዛት የአካባቢ ትብብሮች ማውጫ ለማግኘት፣ በ https://ncadv.org/state-coalitions ለጸረ የቤተሰብ ጥቃት ብሔራዊ ትብብር ይጎብኙ።

## አገልግሎቶች እና ግብዓቶች

- **የጥፋት ጭንቀት የእገዛ መስመሩ (Disaster Distress Helpline)** – 1 (800) 985-5990 – ለማኛውም ተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ያስከተለው ጥፋት የተያያዘ የስሜት ጭንቀት ላጋጠማቸው ሰዎች ፈጣን የአስጊ ሁኔታ የምክር አገልግሎት ለማቅረብ የተሰጠ ብሔራዊ ነጻ የስልክ መስመር ነው።
- **ብሔራዊ የቤተሰብ ጥቃት (National Domestic Violence) ነጻ የስልክ መስመር** – https://www.thehotline.org ወይም 1 (800) 799–7233 ወይም TTY 1 (800) 787–3224 – የቤተሰብ ጥቃት ላጋጠመው፣ መረጃ ማግኘት ለሚፈልግ ወይም ጤናማ ያልሆነ ግንኙነታቸውን ለመጠየቅ የሚፈልጉ ማንኛውም ሰዎች ምስጢራዊ ነጻ የስልክ መስመር ነው። በደህንነት በስልክ መናገር የማይችሉ ከሆነ፣ ወደ 1 (866) 331-9474 LOVEIS ብለው ጽሑፍ ይላኩ ወይም የመስመር ላይ ውይይት ለመጀመር የድርገጹን ይጎብኙ።
- **211** – ከማንኛውም ስልክ 211 ይደውሉ ወይም ወደ 211.org ይጎብኙ እና በዚፕ ኮድ ይፈልጉ – በማህበረሰብዎ ውስጥ ወደ አስቸኳይ ጊዜ እገዛ እና ሌሎች አጋዥ አገልግሎቶች የሚያገናኝዎ ነጻ የስልክ መስመር ነው። ሁሉም ጥሪዎች ምስጢራዊ ናቸው፣ ስም የለሽ ሊደረጉ ይችላሉ እናም ደዋዮች ለ 180 ቋንቋዎች የትርጉም አገልግሎቶች መጠየቅ ይችላሉ።
- **ስራ አጥነት መድህን** – www.usa.gov/unemployment – ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ መሆንዎን ይፈትሹ። አዲሱ የፌደራል ህግ የራሳቸውን ስራ ያላቸው ሰራተኞች እና ነጻ ተቋራጮች የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን ይሰጣል፣ ይህም ተጨማሪ በየሳምንቱ $600 ጥቅማ ጥቅሞችን ጨምሮ መንግስት አሁን ለሚሰጠው የሳምንታት ብዛት ተጨማሪ የ 13 ሳምንታት ጥቅማ ጥቅሞችን ያክላል። ተጨማሪ፣ ግዛቶች ከኮቪድ-19 (COVID-19) ጋር የተያያዙ የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ለማቅረብ ፈቃድ አላቸው፣ ለምሳሌ ሰውየው በአደጋ ተጋላጭነት ወይም ኢንፌክሽን ወይም ቤተሰብን ለመንከባከብ ስራ ሲለቅ፣ ኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት አሰሪ ለጊዜው ስራዎችን ያቆማል፣ ይህ ማለት ሰራተኞች ወደ ስራ አይሄዱም ወይም ሰውየው ተወሽቧል ነገር ግን ውሸባው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ሰራ እንደሚመለስ ይጠበቃል ማለት ነው።

- **የስራ መስክ አንድ መዳረሻ የስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች ማግኛ** – [www.careeronestop.org/LocalHelp/UnemploymentBenefits](www.careeronestop.org/LocalHelp/UnemploymentBenefits) – በግዛትዎ ውስጥ ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ይወቁ።
- **የኢኮኖሚክ ተጽዕኖ ክፍያዎች (Economic Impact Payments)** – [https://www.irs.gov/coronavirus/get-my-payment](https://www.irs.gov/coronavirus/get-my-payment) – ከ $1,200 እስከ $2,400 (ብቁ ከሆኑ ጥገኞች የበለጠ) ለኢኮኖሚክ ተጽዕኖ ክፍያ ብቁ መሆንዎን ይጠይቁ።
- **ነጻ የታክስ ዝግጅት** – [https://irs.treasury.gov/freetaxprep](https://irs.treasury.gov/freetaxprep) – የታክሲዎችዎ ፋይል ለማድረግ በሰለጠኑ በጎ አድራጊዎች የሚሰጠውን ነጻ እገዛ ያግኙ።
- **የማህበረሰብ እርምጃ ወኪል (Community Action Agency)** – [https://communityactionpartnership.com/find-a-cap/](https://communityactionpartnership.com/find-a-cap/) – ምን ዓይነት አገልግሎቶችን (እንደ ለኪራይ ወይም መገልገያዎች የአስቸኳይ ጊዜ ክፍያ እገዛ የመሳሰሉ) እንደሚሰጡ የአካባቢዎ የማህበረሰብ እርምጃ ወኪልን ያነጋግሩ።
- **በክፍያዎች እገዛ** – [www.usa.gov/help-with-bills](www.usa.gov/help-with-bills) – ለቤት ኤነርጂ ክፍያዎች እና ሌሎች ወጪዎችን ክፍያ ለማገዝ ስለ መንግስት መደቦች ይወቁ።
- **ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እገዛ (TANF)** – [https://www.benefits.gov/benefit/613](https://www.benefits.gov/benefit/613)
- **የልጆች እንክብካቤ** - [https://www.childcare.gov/covid-19](https://www.childcare.gov/covid-19) - የልጅ እንክብካቤ ለማግኘት እገዛን አካቶ፣ ስለ ልጅ እንክብካቤ ግብዓቶች በግዛትዎ ውስጥ ያቀርባል።
- **በ COVID-19 ምክንያት ወዲያውኑ የሚገኙ ስራዎች** – [https://needajobnow.usnlx.com](https://needajobnow.usnlx.com) –አሁን መሙላት የሚፈልጉ በታዎችን ከተረጋገጡ አሰሪዎችን ዝርዝር ስራዎችን የሚያቀርብ የድር ጣቢያ ነው።